# እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 21-30/2018 የነበረው

# የአየር ሁኔታ ግምገማ


ባለፉት የሴፕቴምበር ሶስተኛው አሥር ቀናት ለዝናብ መፈጠር አስተዋጽኦ የሚያደርጉ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በተለይም ከመካከለኛው፣ ከሰሜን፣ ከሰሜን ምሥራቅና ከሰሜን ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ እየተዳከሙ በመምጣታቸው ለጥቂት ቀናት ከተስተዋለው ቀላል ዝናብ በስተቀር በአብዛኛው ደረቃማ የአየር ሁኔታ አመዝኖ ቆይቷል፡፡ በአንፃሩ የክረምቱን ዝናብ ሲያገኙ በቆዩት በምዕራብ ጫፍ የሀገሪቱ ክፍሎች እንዲሁም ደግሞ ወደ ሀገሪቱ ደቡባዊ ክፍል በመጠኑም ቢሆን ዝናብ እየጨመረ መሄዱ የበጋው ወቅት ቀስ በቀስ መጀመሩን ያሳያል። ባለፉት አሥር ቀናት አልፎ አልፎ በአንዳንድ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ዝናቡ ከሞላ ጎደል ቀጥሎ የተስተዋለ ሲሆን፤ ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ እንደተመዘገበ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ ከባድ ዝናብ ከመዘገቡ ቦታዎች መካከል ለመጥቀስ ያህል በአየሁ 34.4፣ በቻግኒ 32.9፣ በጋምቤላ 43.0፣ በጎሬ 43.0፣ በማንኩሽ 73.0፣ በማሻ 32 እንዲሁም በከማሺ 48.0 በሚ.ሜ ይገኙበታል።

በአጠቃላይ ባለፉት አሥር ቀናት በትግራይ፣ በአማራ፣ በቤንሻንጉል-ጉሙዝ፣ በጋምቤላ፣ በአብዛኛው ኦሮሚያ፣ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል እና በደቡብ ሶማሌ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቧል።


ባለፉት አስር ቀናት የነበረው ዝናብ ከሀገሪቱ የቦታ ሽፋን አንጻር ሲገመገም ከትግራይ የምዕራብ፣ የምስራቅና የደቡብ ትግራይ፤ ከአማራ አገውአዊ፣ ሰሜንና ደቡብ ጎንደር፣ ባህርዳር፣ ምዕራብ ጎጃምና የኦሮሚያ ልዩ ዞን፤ ቤንሻንጉል-ጉሙዝ፤ ጋምቤላ፤ የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል፤ ከኦሮሚያ ከምዕራብ ሸዋ ዞኖች በስተቀር ሁሉም ዞኖች እንዲሁም አዲስ አበባ ከ5-82 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ2-7 ቀናት ያህል ያገኙ ሲሆን፤ የተቀሩት የሀገሪቱ ስፍራዎች ደረቅ ሆነው ሰንብተዋል (ካርታ 1 እና 2) ፡፡

ባለፉት አስር ቀናት የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር ሲነጻጻር ከትግራይ የመቀሌና የደቡብ ትግራይ፤ ከአማራ የዋግህምራና የሰሜን ጎንደር ምዕራባዊው ክፍል፤ ከኦሮሚያ የቦረናና የጉጂ ዞኖች እንዲሁም ከሶማሌ የጎዴ፣ የቆራሂ፣ የዋርዴርና የአፍዲር ዞኖች መደበኛና ከመደበኛ በላይ የሆነ የዝናብ መጠን የነበራቸው ሲሆን፤ የተቀሩት የሀገሪቱ ክፍሎች ከመደበኛ በታች የሆነ የዝናብ መጠን ነበራቸው (ካርታ 3) ፡፡


ካርታ 1   ኢ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 21 እስከ 30 /2018 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ



ካርታ 2     ኢ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 21 እስከ 30 /2018 ድረስ የነበረው የዝናብ ቀናት




ካርታ 3   እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 21 እስከ 30 /2018 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር



# እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 21-30/2018 የነበረው የአየር ሁኔታ በእርሻ ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተጽዕኖ

ባሳለፍነው የሴፕቴምበር ሶስተኛዉ አስር ቀናት የእርጥበቱ ሁኔታ በአብዛኛው ከመካከለኛው፣ ከሰሜን፣ ከሰሜን ምሥራቅና ከሰሜን ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ እየተዳከሙ በመምጣታቸው ለጥቂት ቀናት ከተስተዋለው መጠነኛ እርጥበት በስተቀር በአብዛኛው ደረቃማ የአየር ሁኔታ ተስተውሏል፡፡ ይህም ሁኔታ ዘግይተው ለተዘሩ፣ ፍሬ በመሙላትና በአበባ ደረጃ ለሚገኙ የተለያዩ ሰብሎች የውኃ ፍላጎታቸውን ሙሉ ለሙሉ ለማሟላት መጠነኛ የእርጥበት እጥረት እንዳጋጠማቸው መገመት ይቻላል፡፡ በተለይም ተጨማሪ የውኃ አቅርቦት ባልነበራቸውና ውኃ የመሸከም አቅማቸው ዝቅተኛ የሆነ የአፈር ይዘት ባላቸው አካባቢዎች የእርጥበት እጥረቱ አሉታዊ ጎን ነበረዉ፡፡ በተጨማሪም የነበረው ሁኔታ በተለይም በሰሜንና በሰሜን ምስራቅ ለሚገኙ የአርብቶ አደርና የከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች የአረንጓዴ ዕፅዋትንና የመጠጥ ውኃ አቅርቦትን ከማሻሻል አኳያ አሉታዊ ጎን ነበረው፡፡ በአንፃሩ የክረምቱን ዝናብ ሲያገኙ በቆዩት በምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች እንዲሁም ደግሞ ወደ ሀገሪቱ ደቡባዊ ክፍል በመጠኑም የቀጠለው እርጥበታማ ሁኔታ እድገታቸውን ላልጨረሱና በተለያየ እድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ ሰብሎችም ሆነ ለቋሚ ተክሎች አዎንታዊ ሚና ነበረው፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ ባለፉት የክረምት ወራት በመደበኛ ሁኔታ ደረቅ ለነበሩትና በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት ደቡባዊ ክፍል በመጠኑም ቢሆን የእርጥበት ሁኔታቸው እንደተሻሻለ የተሰበሰቡና የተተነተኑ የአግሮሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ ይህም ሁኔታ በአካባቢዎቹ የነበረውን ደረቅ ሁኔታ ከማስታገስና የግጦሽ ሳርና የመጠጥ ውኃ አቅርቦትን ከማሻሻል አንጻር በጎ ሚና ነበረው (ካርታ 4)፡፡


ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 21 እስከ 30/2018 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



## እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 21-30/2018 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

እ.ኤ.አ ከ21-30 ሴፕቴምበር 2018 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ የነበረውን ተፅዕኖ ስንመለከት ጥቂት የታችኛው የአባይ፣ ተከዜ፣ የላይኛውና መካከለኛው ባሮአ ኮቦ፣ የመካከለኛውና የታችኛው ኦሞ ጊቤ፣ አብዛኛው ገናሌ ደዋ ተፋሰሶች ከእርጥበታማ እስከ ከፍተኛ እርጥበት ያገኙ ሲሆን፤ መካከለኛው አባይ፣ አብዛኛው ስምጥ ሸለቆና ዋቢ ሸበሌ ተፋሰሶች ከከፊል ደረቅ እስከ መጠነኛ እርጥበት እንደነበራቸው መረጃችን ያመለክታል፡፡ የተቀሩት የሀገሩቱ ተፋሰሶች ደረቃማ ሁኔታ ላይ ሰንብተዋል፡፡ ይህም ሁኔታ ለተለያዩ የኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች አዎንታዊ የሆነ ተፅዕኖ ነበረው (ካርታ 5)፡፡

ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 21 እስከ 30/2018 ድረስ በተፋሰሶች ላይ የነበረው የእርጥበት መጠን



# እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1-10/2018 የሚኖረው

# የአየር ሁኔታ አዝማሚያ

በመጪዎቹ አሥር ቀናት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በአብዛኛው በደቡብና በምዕራብ አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተሻለ ገጽታ ሊኖራቸው እንደሚችል የትንበያ መረጃዎች ያሳያሉ። በዚህም መሰረት ቀደም ብሎ የጀመረው የክረምት ወቅት ዝናብ በምዕራብ አጋማሽ ላይ የሚቀጥል ሲሆን፤ በተጨማሪም ወደ ደቡብና ደቡብ ምሥራቅ ኢትዮጵያ ሊስፋፉ እንደሚችል የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ።

በዚህም መሰረት በሚቀጥሉት አሥር ቀናት በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የበጋው ደረቃማ የአየር ሁኔታ እንደሚያመዝን የሚጠበቅ ሲሆን፤ አልፎ አልፎም ከሚኖረው እርጥበታማ የአየር ሁኔታ የተለያዩ ቦታዎች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ሊያገኙ ይችላሉ።

በአጠቃላይ በሚቀጥሉት አሥር ቀናት ከኦሮሚያ ክልል ጅማ፣ ኢሉአባቦራ፣ ምዕራብ እና ምሥራቅ ወለጋ፣ የቦረናና የጉጂ ዞኖች፤ አዲስ አበባ፤ ከሶማሌ ክልል ሲቲ፣ ጅግጅጋ፣ ደጋሀቡር፣ ፊቅ፣ እና ጎዴ፤ ከደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል ደግሞ የወላይታ፣ የዳውሮ፣ ጋሞጎፋ፣ የከፋና የቤንች ማጂ፣ ጥቂት የሰገን ህዝቦች፤ ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል የአሶሳና የከማሺ ዞኖች፤ ከጋምቤላ ዞን 1፣ 2 እና 4፤ ከአማራ ክልል፣ ምዕራብ ጎጃም፣ እንዲሁም የባህር ዳር ዙሪያ እና አገው አዊ፤ በአብዛኛው ከመደበኛ ጋር የተቀራረበ ዝናብ እንደሚያገኙ ይጠበቃል። በተጨማሪም አርሲና ባሌ፣ ምሥራቅ ሐረርጌ፣ ድሬዳዋና ሐረሪ፣ አልፎ አልፎ ከሚፈጠሩ ደመናዎች አነስተኛ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ። የተቀሩት የሀገሪቱ ሥፍራዎች ደረቅ ሆነው ይቆያሉ።

# እ. ኤ. አ ከኦክቶበር 1-10/2018 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

ከላይ በትንበያው ላይ እንደተገለፀው በመጪዎቹ የኦክቶበር የመጀመሪያዉ አስር ቀናት የእርጥበት ሁኔታው በምዕራብ አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተሻለ እንደሚሆን የሚጠበቅ ሲሆን፤ ይህም ሁኔታ በአብዛኛው ለግብርናው ዘርፍ ጠቀሜታ እንደሚኖረዉ ይጠበቃል፡፡ በመሆኑም ቀደም ብለው ለተዘሩና ፍሬ በማፍራት ላይ ለሚገኙ፣ በተለያየ ምክንያት ዘግይተው ለተዘሩና በተለያየ እድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ ሰብሎችም ሆነ ለቋሚ ተክሎች የተሟላ እድገት የሚያስፈልጋቸውን የውኃ አቅርቦት ከማረጋገጥ አንፃር አዎንታዊ ሚና ይኖረዋል፡፡ በተጨማሪም በዚህ ጊዜ የሚገኘዉ እርጥበት ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት ለደቡባዊው የሀገሪቱ ክፍሎች ደጋማ አካባቢዎች የማሳ ዝግጅት ለማድረግና ዘር ለመዝራት ምቹ ሁኔታ እንደሚፈጥር የሚጠበቅ ሲሆን፤ የእርጥበት ሁኔታው ወደ ደቡብና ደቡብ ምስራቅ የሚያደርገው መስፋፋት ለአርብቶ አደርና ለከፊል አርብቶ

አደር አካባቢዎች ጥሩ ጎን ይኖረዋል፡፡ በሌላ በኩል ውኃ አጠር የሆኑ አካባቢዎች የሚገኘውን የዝናብ ውኃ ለመሰብሰብና ለማከማቸት መልካም አጋጣሚ ስለሚያገኙ ይህንኑ ለማከናወን የሚያስችል ዝግጅት እንዲያደርጉ ይመከራሉ፡፡ በተጨማሪም በአንዳንድ አካባቢዎች ላይ ሰብሎች እየደረሱ ከመሄዳቸው ጋር ተያይዞ የሰብል ስብሰባ እየተከናወነ ሲሆን፤ የሚጠበቀው እርጥበት ጉዳት እንዳያደርስ በየጣልቃው የሚኖረውን ደረቅ ሰሞነኛ በመጠቀም የደረሱ ሰብሎችን በወቅቱ በማንሳት አስፈላጊውን ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

## እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1-10/2018 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በውሃው ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

የኦክቶበር ወር የበጋው ወቅት የመጀመሪያው ወር ሲሆን፤ በዚህ ወር ውስጥ የበጋው ነፋሻማና ደረቃማው ሁኔታ በአብዛኛው የሀገሪቱ ተፋሰሶች ለይ የሚሰተዋልበት ወቅት ነው፡፡ በሚቀጥሉት የኦክቶበር ወር የመጀመሪያው አስር ቀናት ምዕራብና ደቡብ ምእራብ በሚገኙ ተፋሰሶች ላይ የክረምቱ ዝናብ በተወሰነ መልኩ የሚቀጥል ሲሆን፤ ቀስ በቀስ ወደ ደቡብና ደቡብ ምስራቅ ተፋሰሶች ማለትም ገናሌ ዳዋ፣ ዋቢሸበሌና የኦጋደን ተፋሰሶች ላይ እየተስፋፋ ይሄዳል፡፡ በዚህም መሠረት መካከለኛውና ደቡባዊው አባይ፣ የታችኛው ባሮ አኮቦ፣ መካከለኛውና የታችኛው ኦሞ ጊቤ፣ የታችኛው ሪፍት ቫሊ፣ ምዕራባዊው ገናሌ ዳዋ እንዲሁም የላይኛው ኦጋዴንና መካከለኛው ዋቢ ሸበሌ ተፋሸሾች በአብዛኛው ከመደበኛው ጋር የተቀራረበ የዝናብ መጠን ሊኖራቸው እንደሚችል የትንበያ መረጃው ያመላክታል፡፡ እንዲሁም ጥቂት የላይኛው ዋቢ ሸበሌና ገናሌ ዳዋ ተፋሰሶች አልፎ አልፎ መጠነኛ የዝናብ መጠን ሊኖራቸው ይችላል፡፡ ይህም ሁኔታ በተለይ ደቡብ ምእራባዊ ተፋሰሶች ላይ ለመሰኖ ስራና ለመጠጥ ውሃ የተሻለ ጥቅም ስለሚኖረው የሚመለከተው አካል በተቻለ መጠን የሚገኘውን ውሃ በአግባቡ መጠቀም እንዳለበት ለማሳሰብ እንወዳለን፡፡